# የስድስተኛ ክፍል የአካባቢ ሳይንስ የሞዴል ፈተና መለማመጃ ጥያቄዎች

## ቁጥር ሁለት

1. የአየር ንብረት ተቆጣጣሪ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ) ኬክሮስ ለ) ከፍታ ሐ) የሙቀት መጠን መ) የውቅያኖስ ሞገድ

2. አክሱማውያን የፈጠሩት ፊደላት ምን በማባል ይታወቃል?

ሀ) የሳባውያን ለ) ግ ዕዝ ሐ) አማርኛ መ) ኩሽ

3. ምስራቅ አፍሪካ ከአፍሪካ ካሉ ሌሎች ቀጠናዎች በህዝብ ብዛት ስንተኛ ደረጃ ይይዛል?

ሀ) አንደኛ ለ) ሦስተኛ ሐ) አራተኛ መ) ሁለተኛ

4. በምስራቅ አፍሪካ በህዝብ ቁጥር ከፍተኛዋ ሃገር ማናት?

ሀ) ኢትዮጵያ ለ) ሲሸልስ ሐ) ኤርትራ መ) ሁሉም

5. በምስራቅ አፍሪካ ከተነሱት ታላላቅ እና ቀደምት ስልጣኔዎች ውስጥ ይመደባሉ ::

ሀ) የኑቢያ ስልጣኔ ለ) የአክሱም ስልጣኔ ሐ) ሀ እና ለ መ) ሁሉም

6. ከሚከተሉት ውስጥ የምስራቅ አፍሪካ ብሔራዊ ፓርክ ያልሆነው የቱ ነው ?

ሀ) ማሳይ ማራ ለ) ደንክል በረሃ ሐ) አዋሽ መ) አላንካ

7. ከኢትዮጵያ የማይወጣው ወንዝ የቱ ነው?

ሀ) ባሮ ለ) አዋሽ ሐ) አባይ መ) ሁሉም

8. ከሚከተሉት ሐይቆች ውስጥ ሰው ሰራሽ ሐይቅ የሆነው የቱ ነው?

ሀ) ካቦራባሳ ለ) ጣና ሐ) ዝዋይ መ) ላንጋኖ

9. የኑቢያ ስልጣኔ የመጀመሪያው ዋና ከተማ ማን ይባላል?

ሀ) ናፓታ ለ) አክሱም ሐ) ግብፅ መ) መልስ የለም

10. ከአለቶች የተሰራ የላይኛው የመሬት ክፍል ምን ይባላል?

ሀ) ማዕድን ለ) አፈር ሐ) ውሃ መ) ደን

LIVEWORKSHEETS

11. ደን ባልነበረ ቦታ ዕፅዋት መትከል ምን ይባላል?

ሀ) ደንና　　ለ) ዳገመ ደንና　　ሐ) ጣምራ የደን እርሳ　　መ) የእርከን ስራ

12. ቅጠለ ሰፋፊ የዛፍ ዓይነቶች የሚበቅሉጥ................ሜትር ከፍታ ባላቸው ቦታዎች ነው::

ሀ) ከ 1,300 እስከ 4,000　　ለ) ከ 1,500 እስከ 1,800

ሐ) ከ 2,200 እስከ 3,000　　መ) ከ 410 እስከ 1,000

13. ከሚከተሉት አማራጮች የወንዝ ጥቅም የቱ ነው?

ሀ) ለቱሪዝም　　ለ) ለዓሳ ምርት　　ሐ) ለመጓጓዣ　　መ) ሁሉም

14. ከሚከተሉት ውስጥ በሞቃታማ አየር ንብረት ክልል አካባቢ በብዛት የሚገኘው የዛፍ ዓይነት የቱ ነው?

ሀ) ጥድ　　ለ) ሾላ　　ሐ) ዝግባ　　መ) ግራር

15. አጠቃላይ የመሬት ክፍል .............. በሙቶ የሚሆነው የመሬት ገፅ በውሃ የተሸፈነ ነው?

ሀ) 97　　ለ) 30　　ሐ) 70　　መ) 20

16. ካምቢሶል እና ላቪሶል የአፈር ዓይነቶች በየትኛው የምስራቅ አፍሪካ ሀገር የሚገኙ ናቸው?

ሀ) በኬን ያ　　ለ) በሶማሊያ　　ሐ) በኢትዮጵያ　　መ) በሩዋንዳ

17. ................. ከፍታቸው ከ 2000 ሜትር በላይ በሆኑ አካባቢዎች ይበቅላል?

ሀ) የዝግባ ዛፎች ደን　　ለ) የቅጠለ ሳፋፊ ዛፎች ደን

ሐ) የውርጭ ዛፎች ደን　　መ) የሞቃታማ በረሃ እፅዋት

18. በደቡባዊ አረቢያ ላይ ከፍተኛ ዘመቻ ያደረገ የአክሱም ንግጉስ ማነው?

ሀ) ንጉስ ካሌብ　　ለ) ንጉስ ኢዛና　　ሐ) ንጉስ ላሊበላ　　መ) ሁሉም

19. ለመጠጥነት የሚያገለግለው የውሃ መጠን ከአጠቃላይ የውሀ መጠን........... ነው::

ሀ) 3 %　　ለ) 2 %　　ሐ) 5 %　　መ) 1 %

20. ከሚከተሉት ውስጥ የተፈጥሮ ሐብት እንክብካቤ ዘዴ የሆነው የቱ ነው?

ሀ) ታዳሽ የሀይል ምንጮችን መጠቀም　　ለ) ሀገር በቀል እፅዋትን መትከል

ሐ) የተፈጥሮ ሀብትን ባግባቡ መጠቀም　　መ) ሁሉም

LIVEWORKSHEETS

21. ከሚከተሉት የአፈር ዓይነቶች አንዱ ኢትዮጵያ ውስጥ አይገኝም::

ሀ) ኒቶ ሶል ለ) ሊቶሶል ሐ) ካምቢሶል መ) ቨርቲ ሶል

22. በኢትዮጵያ ለመጓጓዣነት የሚያገለግለው ብቸኛው ወንዝ ማን ነው?

ሀ) አባይ ለ) ተከዜ ሐ) ባሮ መ) አዋሽ

23. ስለ ሰው ሰራሽ ማዳበሪያ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ) የአፈርን ምርታማነት ለመጨመር ያገለግላል ለ) በተፈጥሮ ከሚገኙ ተረፈ ምርቶች ይሰራል

ሐ) በፋብሪካ ከተለያዩ ኬሚካሎች ይሰራል መ) ሁሉም

24. ውሃ ............. እና ............. ንጥረ ነገሮች በኬሚካላዊ መንገድ በመዋሃድ የሚፈጥሩት የተፈጥሮ ሃብት ነው::

ሀ) ሀይድሮጅን እና ኦክስጅን ለ) ሃይድሮጅን እና ናይትሮጅን

ሐ) ሃይዲሮጂን እና ካርበንዳይ ኦክሳይድ መ) ኦክሲጂን እና ናይትሮጂን

25. ከሚከተሉት ውስጥ ለአፈር መሸርሸር ምክንያት የሆነው የቱ ነው?

ሀ) አግድም ማረስ ለ) እርከን መስራት

ሐ) ቁልቁል ማረስ መ) የእፅዋት ሽፋን መጨመር

26. ከሚከተሉት ውስጥ መንፈሳዊ ቅርስ የሆነው የቱ ነው ?

ሀ) ሃውልቶች ለ) ህንፃዎች

ሐ) የሃይማኖት እና የእምነት ሥነ ስርዓት መ) የጦር መሳሪያዎች

27. የአለማችን ረጅሙ ወንዝ ማነው?

ሀ) አዋሽ ለ) ናይል ሐ) ጫሞ መ) ገናሌ

28. ደም የሚረጨው የሰውነታችን አካል የቱ ነው?

ሀ) ሳንባ ለ) አፍ ወና

ሐ) ልብ መ) የደም ስር

LIVEWORKSHEETS

29. በደቂቃዎችና በሰዓታት የሚቀያየር የአየር ፀባይ ------- ይባላል::

ሀ) የአየር ንብረት　　ለ) የአየር ግፊት

ሐ) የአየር ሁኔታ　　መ) ሁሉም

30. ከሚከተሉት ውስጥ ትክክል የሆነው የቱ ነው ?

ሀ) ልብ በሰውነታችን ውስጥ በስተቀኝ ደረታችን አካባቢ ትንሽ ዝቅ ብሎ የሚገኝ በጡንቻዎች የተገነባ የውስጥ አካል ክፍል ነው::

ለ) የአየር ንብረት ለረዥም ጊዜ የሚከሰት አማካይ የአየር ፀባይ ድምር ውጤት ነው::

ሐ) የውቅያኖስ ሞገድ የአየር ንብረት ተቆጣጣሪ ነው::

መ) ከፍታ ሲጨምር የሙቀት መጠንም ይጨምራል::

ሠ) ለ እና ሐ

31. ደም ለማረጋት የሚጠቅመው የደም ህዋስ የቱ ነው

ሀ. ነጭ የደም ህዋስ　　ለ. ቀይ የደም ህዋስ

ሐ. ፕላትሌቶች.　　መ. ደምቅዳ

32. ሁለት ፍሳሾችን ባላቸው የነጥበ ፍሌት ልዩነት የምንለይበት የመለያ ዘዴ የትኛው ነው

ሀ. ትነት.　　ለ. በረራ.　　ሐ. ጥሊያ　　መ. ንጥረት

33. ወደ አብይ ትንቧ ለሚገባወና ለሚወጣው አየር መተላለፊያ ሆኑ የሚገለግልው የቱ ነው

ሀ. ዐብይ ትንቧ.　　ለ. ድህረ አፍ　　ሐ. ስረን.　　መ. ደቂቅ ትንቧ

34. በጉረምስና ወቅት በወንዶች ላይ የሚይታይ አካላዊ ለወጠ የቱ ነው

ሀ. ጡንቻዋች ይዳብራሉ　　ለ. የድምፅ መጎርነን.

ሐ. የትካሻና ደረት መስፋት　　መ ሁሉም

LIVEWORKSHEETS

35. ውህና አልሚ ምግቦችን የሚይዝ የደም ክፍል ነው

ሀ. የደም ዑደት ለ. ፐላዝማ

ሐ. ደም መልስ መ ደም ቅዳ

36. ሁል ጊዜ ያለ ማቋረጥ በስራ ላይ የሚገኘው የሰውነታችን ክፍል የቱ ነው

ሀ. ሳንባ ለ. ልብ. ሐ. አፍ መ. አይን

37. ....... አየር እና ምግብ በጋራ የሚተላለፍበት የስርዓተ ትንፈሳ አካል ነው ::

ሀ) ትንክረት ሐ) ደቂቅ ትንቧ

ለ) ባላትንቧ መ) ድህረ አፍ

38. ከሚከተሉት ውስጥ ስለምጋት እና ኢምጋት ትክክል ያልሆነው የቱ ነው ?

ሀ) የውሃ ትነት በምጋት፣ዝቅተኝ በኢምጋት ከፍተኛ

ለ) ሙቀት በምጋት ዝቅተኛ፣ በኢምጋት ከፍተኛ

ሐ) ሙቀት በምጋት ከፍተኛ፣ በኢምጋት ከፍተኛ

መ) ናይትሮጅን በምጋት 78% ፣ በኢምጋት 78 %

39. የትኛው የሰርዓተ ትንፈሳ ክፍል ነው ቅርጹን በመቀያየር ሳንባችን በስርዓት እንድንተነፍስ የሚያስችለው

ሀ) ድልሺ ለ) ሰርን ሐ) ትንክረት መ) አፍወና

40. የአብይ ቋሚ መስመር ስንት ድግሪ ላይ ይገኛል?

ሀ. 90. ለ. 60 ሐ. 0 መ. 180

LIVEWORKSHEETS